የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ

ETHIOPIAN TELECOMMUNICATION AGENCY

# የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ሪሴል እና የቴሌሴንተር ፍቃድ መመሪያ

ጥቅምት 29 ቀን 1995

አዲስ አበባ

www.chilot.me

የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን ለማዳረስ የሪሴልና የቴሌሴንተር አገልግሎቶችን ማስፋፋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተለይ ደግሞ የቴሌሴንተር መቋቋም ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባልተደረሰባቸው ቦታዎች አገልግሎቱን ለማዳረስ ስለሚያስችል፣

የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 49/1989 (እንደተሻሻለው) አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

# አንቀጽ አንድ

## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ሪሴል እና የቴሌ ሴንተር ፍቃድ መመሪያ ቁጥር 1/1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

# አንቀጽ ሁለት

## ትርጓሜ

በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 (እንደተሻሻለው) እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 47/1991 የተመለከቱት ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያ ላይ ተፈጻሚ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1. "ሚኒስቴር" ማለት የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር ነው።

2. "ኤጀንሲ" ማለት የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ ነው።

3. "የስልክ ሪሴል አገልግሎት" ማለት በአንድ ከተማ ውስጥ ለሚደረግ ጥሪ (Local call) ወይም ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ለሚደረግ ጥሪ (Long distance call) ወይም አለምአቀፍ ጥሪ (International call) ለሦስተኛ ወገን የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል በቋሚ ወይንም ተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል) የማስደወል አገልግሎት ሲሆን በልዩ ስምምነት መልእክት የመቀበል አገልግሎትን ያጠቃልላል።

4. "የፋክስ ሪሴል አገልግሎት" ማለት ለሦስተኛ ወገን የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል መልእክት በፋክስ አማካይነት የመላክ ወይም የመቀበል አገልግሎት ነው።

5. "የኢንተርኔት ሪሴል አገልግሎት" ማለት ለሦስተኛ ወገን የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል ኢንተርኔት ብራውዝ የማስደረግ ወይም ኢ-ሜይል የመላክና የመቀበል አገልግሎት ነው።



www.chilot.me

6. "ቴሌሴንተር" ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የቴሌኮሙኒኬሽን ሪሴል አገልግሎቶች በአንድ ላይ የሚሰጡበት ማዕከል ነው።

7. "ሪሴለር" ማለት ከኤጀንሲው ፍቃድ በማውጣት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሪሴል የሚያደርግ ወይም ቴሌሴንተር ያቋቋመ ሰው ነው።

8. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

9. "ኮርፖሬሽን" ማለት በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 /እንደተሻሻለው/ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት ብቸኛ የሆነው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ተብሎ ትርጓሜ የተሰጠው አካል ነው።

# አንቀጽ ሶስት

# የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ በትርፍ ላይ ባልተሰማራ ሰው ላይም ተፈጻሚነት ይኖረዋል። ሆኖም በትርፍ ላይ ያልተሰማራው ሰው የሚያስከፍለው የአገልግሎት ዋጋ ኮርፖሬሽኑ ከሚያስከፍለው በላይ መሆን አይችልም።

# አንቀጽ አራት

# ለሪሴል የተፈቀዱ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች

ለሪሴል የተፈቀዱ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች የስልክ፣ የፋክስ ወይም የኢንተርኔት አገልግሎቶች ናቸው።

# አንቀጽ አምስት

# ፍቃድ

1. በዚህ መመሪያ መሠረት የተፈቀዱ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን ሪሴል ለማድረግ ወይም የቴሌሴንተር ለማቋቋም የሚፈልግ ሰው በዚህ መመሪያ መሰረት ፍቃድ የማውጣት ግዴታ አለበት።

2. ፍቃዱ የሚያገለግለው በፍቃዱ ላይ ለተገለፀው የሪሴል ወይም የቴሌሴንተር አገልግሎት እና በፍቃዱ ላይ በተጠቀሰው አድራሻ ውስጥ ለሚሰጥ አገልግሎት ብቻ ነው። በፍቃዱ ላይ ከተጠቀሰው አድራሻ በተጨማሪ በሌላ አድራሻ የሪሴል ወይም የቴሌሴንተር አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ሰው በእያንዳንዱ አድራሻ ፍቃድ ማውጣት አለበት።



www.chilot.me

3. ለአንድ የሪሴል አገልግሎት ፍቃድ የወሰደ ሰው አንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሪሴል የተፈቀዱ አገልግሎቶች በተጨማሪ መስጠት ቢፈልግ የቴሌሴንተር ፍቃድ ማውጣት አለበት።

4. የዚህ መመሪያ አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 6 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቴሌሴንተር ፍቃድ ያለው ሰው ኤጀንሲው ጋር መቅረብ ሳያስፈልገው መስጠት ያልጀመረውን የሪሴል አገልግሎት በኋላ ለመጀመር ይችላል።

# አንቀጽ ስድስት

# ፍቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1. ለስልክ ሪሴል አገልግሎት ፍቃድ ለማግኘት የሚፈልግ አመልካች ቢያንስ፦

   ሀ) አንድ የስልክ መስመር፣

   ለ) እያንዳንዱ ተገልጋይ የሚጠቀምበትን ጊዜ ወይም ዋጋ የሚያሳይ ከስልኩ ጋር አብሮ የተገጠመም ይሁን ከውጭ ብቻውን የሚገጠም መሣሪያ ማሟላት አለበት።

2. የፋክስ ሪሴል አገልግሎት ፍቃድ ለማግኘት የሚፈልግ አመልካች ቢያንስ አንድ የፋክስ ማሽን፣ የስልክ መስመር እና ከፋክስ ማሽኑ ጋር አብሮ የተሰራም ይሁን ከውጭ ብቻውን የሚገጠም፣ ተገልጋዩ የተጠቀመውን የአገልግሎት ጊዜ ወይም ዋጋ የሚያሳይ መሳሪያ ማሟላት አለበት።

3. የኢንተርኔት ሪሴል አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ አመልካች ቢያንስ፦

   ሀ/ አንድ የኢንተርኔት አካውንት

   ለ/ ኢንተርኔት ብራውዝ ለማድረግና ኤሌክትሮኒክ ሜይል ለመላክ ወይም ለመቀበል የሚያስችል ሶፍት ዌር የተገጠመለት አንድ ኮምፒዩተር እና ሞደም፣

   ሐ/ አንድ ፕሪንተር፣

   መ/ ተገልጋዩ የተጠቀመበትን ሰዓትና ዋጋ የሚያሳይ መሣሪያ ማሟላት አለበት።

4. አመልካቹ ቀደም ሲል የሚጠቀምበት የስልክ፣ የፋክስ ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ያለው ሆኖ አንዱን ወይም ሁሉንም አገልግሎቶች ለሪሴል አገልግሎት መጠቀም የሚፈልግ ከሆነ ከኮርፖሬሽኑ ጋር የሪሴል አገልግሎት ውል ማቅረብ አለበት።

5. አመልካቹ ነጋዴ ከሆነ ፍቃድ ለማግኘት በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ከሚመለከተው መሥሪያ ቤት የዋና ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት።

# አንቀጽ ሰባት
# የፍቃድ ማመልከቻ፣ ፍቃድ መስጠትና መከልከል

1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት ፍቃድ ለማግኘት ማመልከቻውን ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት።

2. ማመልከቻው ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘውና አባሪ 1 በሆነው የፍቃድ መጠየቂያ ቅፅ መቅረብ አለበት። የፍቃድ መጠየቂያውን ቅፅ ለስራ አፈፃፀም አመቺ በሆነ ሁኔታ በኤጀንሲው ሊሻሻል ይችላል።

3. አመልካቹ አዲስ የስልክ መስመር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ለማስገባት የኤጀንሲውን ትብብር የሚፈልግ ከሆነ፣ ኤጀንሲው የአመልካቹን ጥያቄ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቱን ሪሴል ለማድረግ በታሰበበት አድራሻ ለሚገኘው የኮርፖሬሽኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከ2 የሥራ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በኢ-ሜይል፣ በፋክስ፣ በፖስታ ወይም በግንባር እንዲደርስ ያደርጋል።

4. ማንኛውም የኮርፖሬሽኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኤጀንሲው በኩል የደረሰውን የስልክ መስመር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ጥያቄ አመልካቹ ማግኘት መቻል አለመቻሉን ደብዳቤው በደረሰው ከ5 የሥራ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው ማስታወቅ አለበት። ኮርፖሬሽኑ መስመር የለም ወይም አገልግሎቱን መስጠት አልችልም የሚል መልስ በሰጠ ጊዜ ኤጀንሲው የዚህኑ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ይችላል።

5. በአመልካቹና በኮርፖሬሽኑ መካከል የሚፈረመው የሪሴል ውል መፈራረሚያ ጊዜ አመልካቹ ውሉን ለመፈረም ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሦስት የሥራ ቀን መብለጥ የለበትም።

6. አመልካቹ፡-
   - ሀ/ ከኮርፖሬሽኑ ጋር የተፈራረመውን ውል፣
   - ለ/ ነጋዴ ከሆነ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የዋና ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣
   - ሐ/ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣
   - መ/ አመልካቹ ለትርፍ ያልተቋቋመ ከሆነ ሕጋዊ ሰውነት ያገኘበት ሰርተፊኬት፣
   - ሠ/ 2 ጉርድ ፎቶግራፎችን ወይም የንግድ ማህበር ከሆነ የሥራ አስኪያጁን 2 ጉርድ ፎቶ ግራፎች፣

   በዚህ መመሪያ አባሪ 1 ውስጥ ከተገለፀው የፍቃድ መጠየቂያ ቅፅ ጋር ሲያቀርብ ኤጀንሲው ፍቃዱን ከአንድ ቀን ባልበለጠ የሥራ ቀን ውስጥ ይሰጠዋል።



www.chilot.me

7. አመልካቹ ለጠየቀው የፍቃድ ዓይነት በዚህ መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በሙሉ ካላሟላ ኤጀንሲው ፍቃዱን ይከለክለዋል። ኤጀንሲው ፍቃዱን የከለከለበትን ምክንያት ከአንድ ቀን ባልበለጠ የሥራ ቀን ውስጥ ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።

# አንቀፅ ስምንት

# የፍቃድ ጊዜ ፣ ክፍያ፣ እድሳትና ፍቃድ ስለመሠረዝ

1. ኤጀንሲው የሚሰጠው ፍቃድ የሚያገለግለው በተሰጠበት ጊዜ ላለው አንድ የመንግስት የበጀት ዓመት ሲሆን በየዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ሐምሌ 30 ድረስ ባሉት ቀናት መታደስ ይኖርበታል።

2. አመልካቹ ፍቃዱን ሲወስድ የሚከተለውን የፍቃድ ክፍያ ለኤጀንሲው ይከፍላል።

   ሀ. የስልክ፣ የፋክስ ወይም የኢንተርኔት የሪሴል አገልግሎት በተናጠል ለመስጠት ለሚፈልግ ሰው ብር 150 /አንድ መቶ ሃምሣ ብር/።

   ለ. ቴሌሴንተር ለማቋቋም የሚፈልግ ሰው ብር 200 /ሁለት መቶ ብር/።

3. አመልካቹ ፍቃዱን በየዓመቱ ሲያሳድስ የሚከተለውን ለኤጀንሲው ይከፍላል።

   ሀ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) ለተገለፀው ብር 30 /ሰላሳ ብር/።

   ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) ለተገለፀው ብር 50 /ሃምሣ ብር/።

4. የዚህ መመሪያ አንቀፅ አስራ አራት ንዑስ አንቀፅ 1 እና 6 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ባለፍቃዱ ፍቃዱን ያገኘው በሀሰት ወይም በተጭበረበረ መረጃ መሆኑን ኤጀንሲው ካረጋገጠ ወይም ባለፍቃዱ ከከሰረ ወይም ስራውን ከተወ ወይም ፍቃዱ መታደስ ያለበት ጊዜ ካለቀ ፍቃዱ ይሰረዛል።

# አንቀጽ ዘጠኝ

# የባለፍቃዱ ግዴታዎች

1. ባለፍቃዱ የዚህን መመሪያና አግባብ ያላቸውን ሕጎች ድንጋጌ የማክበር ግዴታ አለበት።
2. ባለፍቃዱ በፍቃዱ ላይ ከተገለፀው አገልግሎት ውጪ የሪሴል ወይም የቴሌሴንተር አገልግሎት መስጠት አይችልም። የሚሰጠውን የቴሌኮሙኒኬሽን ሪሴል ወይም የቴሌሴንተር የአገልግሎት ዋጋ፣ አገልግሎቱን በሚሰጥበት ቦታ በግልፅ ለተገልጋዮች በሚታይበት ሁኔታ የመለጠፍ ግዴታ አለበት።



www.chilot.me

3. ባለፍቃዱ የሚጠቀምባቸው የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 አንቀፅ 14 መሠረት ኤጀንሲው ፍቃድ የሠጠባቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

4. ባለፍቃዱ የጊዜ ወይም የዋጋ ማሳያው በተበላሸ ወይም በማይሰራ ጊዜ አገልግሎት መስጠት የለበትም።

5. የሪሴል ወይም የቴሌሴንተር ፍቃድ ያለው ሰው ፍቃዱን ከወሰደ በኋላ የሚጠቀምባቸውን የስልክ መስመሮች ወይም ኢንተርኔት አካውንቶች ብዛት መጨመር ይችላል። ሆኖም የጨመረውን የስልክ መስመር ወይም ኢንተርኔት አካውንት ዝርዝር መረጃ ለኤጀንሲው በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።

6. የቴሌሴንተር ፍቃድ ያለው ሰው ሌላ ፍቃድ ሳያስፈልገው ፍቃዱን በወሰደ ጊዜ ካሳወቀው የሪሴል አገልግሎት ሌላ ተጨማሪ የሪሴል አገልግሎት መስጠት መጀመር ይችላል። ሆኖም ስለጀመረው አገልግሎት ያለውን ዝርዝር መረጃ በፅሁፍ ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለበት።

7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5 እና 6 የተገለፀው የማሳወቅ ተግባር ቢዘገይ ፍቃድ በሚታደስበት ጊዜ መከናወን አለበት።

# አንቀፅ አስር

# የአገልግሎት ዋጋ

1. ኮርፖሬሽኑ ለሪሴለሩ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስከፍለው ዋጋ ሌሎች ደንበኞችን ከሚያስከፍለው ዋጋ በላይ መሆን የለበትም።

2. በመደበኛ ስልክ ወደ ሞባይል ለሚደረጉ ጥሪዎች፣ በአንድ ከተማ ውስጥ ለሚደረጉ ጥሪዎች (Local calls)፣ ከአንድ ከተማ ወደሌላ ከተማ ለሚደረጉ ጥሪዎች (Long distance calls) ወይም ለአለምአቀፍ ጥሪዎች (International calls) ሪሴለሩ የዚህ መመሪያ አባሪ 3 በሆነው የታሪፍ ሰንጠረዥ መሠረት ያስከፍላል።

3. የፋክስ፣ የኢንተርኔትና የሞባይል የሪሴል አገልግሎት ዋጋ በሪሴለሩ ይወሰናል::

4. የዚህ መመሪያ አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 3 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ዋጋ ሲለወጥ ኮርፖሬሽኑ ለሪሴለሩ በማስታወቂያ /Public Notice/ ይገልፅለታል::



www.chilot.me

# አንቀጽ አስራ አንድ
# የኮርፖሬሽኑ ግዴታና ኃላፊነቶች

ኮርፖሬሽኑ፦

1. ውል ለተፈራረመው ባለፍቃድ አገልግሎቱን ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ መስመሮችን የመዘርጋት ወይም አገልግሎቶችን የመስጠት ግዴታ አለበት።

2. ሪሴለሩን ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ 2 ሆኖ በተያያዘው የውል ናሙና መሠረት ውል ያስፈርማል።

3. በቋሚ ስልክ ወደ ሞባይል ለሚደረጉ ጥሪዎች፣ በአንድ ከተማ ውስጥ ለሚደረጉ ጥሪዎች፣ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ለሚደረጉ ጥሪዎች እና ለአለም አቀፍ ጥሪዎች የሚያስከፍለውን ታሪፍ የሪሴል ውል በሚፈረምበት ጊዜ ለሪሴለሩ ይሰጣል።

4. ለባለፍቃዱ በተዘረጋው መስመር ወይም አገልግሎት ላይ ብልሽት በሚያጋጥም ጊዜ ቅድሚያ ሰጥቶ በአስቸኳይ ጥገና በማድረግ መስመሩን ለአገልግሎት ዝግጁ የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ይህ የጥገና ጊዜ ከ2 ቀናት መብለጥ የለበትም።

5. በባለፍቃዶች መካከል ልዩነት አያደርግም።

6. ኤጀንሲው የዚህን መመሪያ ተግባራዊነት ለማረጋገጥ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ የመደገፍና ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት። በተለይም ኤጀንሲው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 14 መሠረት ለሚወስዳቸው እርምጃዎች ሙሉ ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት።

# አንቀጽ አስራ ሁለት
# የኤጀንሲው ኃላፊነት

1. ኤጀንሲው በዚህ መመሪያ መሠረት ለሚሰጡ ፍቃዶች ፍቃድ ሰጪና የመመሪያው አስፈጻሚ አካል ነው:: ይህ መመሪያ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ኃላፊነትም አለበት።

2. ኤጀንሲው በዚህ መመሪያ የተጣሉትን ግዴታዎች በተላለፈ ባለፍቃድ ላይ በመመሪያው መሠረት እርምጃ ይወስዳል።



www.chilot.me

3. ኤጀንሲው ቴሌሴንተሮች እንዲስፋፉ ጥረት ያደርጋል።

4. ኤጀንሲው ይህ መመሪያ መከበሩን ለማረጋገጥ በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 አንቀፅ 17 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ባለፍቃዱ አገልግሎቱን በሚሰጥበት ቦታ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል።

5. ኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሌለው አካባቢ በዚህ መመሪያ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች አግባብነት ላላቸው መንግስታዊ ድርጅቶች ውክልና በመስጠት ለማሰራት ይችላል።

# አንቀጽ አስራ ሦስት

# ክልከላ

1. ባለፍቃዱ በዚህ መመሪያና ኮርፖሬሽኑ ጋር በሚገባው ውል ላይ ከተዘረዘሩት የአገልግሎት ዓይነቶች ውጪ ኮርፖሬሽኑ የዘረጋውን መስመር ተጠቅሞ ሌላ አገልግሎት መስጠት አይችልም።

2. ኢንተርኔትን በመጠቀም የድምፅ ወይም የፋክስ መልእክትን ማስተላለፍ ወይም የማስተላለፍ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው።

3. ባለፍቃዱ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ኮምፒዩተሮቹን በኔትወርክ በማያያዝ ከአንድ በላይ ለሆኑ ተገልጋዮች የኢንተርኔት ሪሴል አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ በአንድ የኢንተርኔት አካውንት በመጠቀም የሚያያዙት ኮምፒዩተሮች ብዛት ከአምስት በላይ መብለጥ የለበትም። ሆኖም ይህ ገደብ ባለፍቃዱ ከኮርፖሬሽኑ በሚወስደው የሊዝድ (ዴዲኬትድ) መስመር የኢንተርኔት ሪሴል አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ በሊዝድ (ዴዲኬትድ) መስመሩ ላይ በሚያያይዛቸው ኮምፒዩተሮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

4. የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲሰጥበት ከተፈቀደ ስፍራ ውጪ ኬብልም ሆነ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ በመጠቀም፣ የሪሴል አገልግሎት ደንበኞች የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ የተከለከለ ነው።

# አንቀጽ አስራ አራት

# የወንጀልና የፍትሐብሄር ኃላፊነት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ወይም አንቀጽ 13 ላይ የተመለከቱትን የተላለፈ ባለፍቃድ በኤጀንሲው ፍቃዱ ይሰረዝበታል። በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ ለሪሴል አገልግሎቱ የሰጠው መስመር እንዲቋረጥበት ይደረጋል።



www.chilot.me

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህን መመሪያ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተላለፈ ባለፍቃድ በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በወንጀሉ ይጠየቃል።

3. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ ያለፍቃድ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን ሪሴል ሲያደርግ የተገኘ ሰው ከኮርፖሬሽኑ የሚያገኘው አገልግሎት እንዲቋረጥበት ይደረጋል። በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በወንጀሉ ይጠየቃል።

4. ይህን መመሪያ በመተላለፍ ባለፍቃዱ በኮርፖሬሽኑ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት፣ ባደረሰው ጉዳት መጠን የፍትሐብሄር ኃላፊነት አለበት::

5. ይህን መመሪያ በመተላለፍ ፍቃዱ የተሰረዘበት ሰው በኮርፖሬሽኑ ላይ ባደረሰው ጉዳት መጠን በኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ሕግ መሠረት ለኮርፖሬሽኑ ካሳ ከከፈለ ከአንድ አመት በኋላ የቴሌኮሙኒኬሽን ሪሴል አገልግሎት ውል ከኮርፖሬሽኑ ጋር ከተፈራረመ፣ ኤጀንሲው ፍቃድ ሊሰጠው ይችላል::

6. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 4 በተገለፀው መሠረት የኤጀንሲውን ምርመራ የማድረግ ስልጣኑን ያደናቀፈ ወይም ለማስተጓጐል የሞከረ ባለፍቃድ ፍቃዱ ይሠረዝበታል። ከኮርፖሬሽኑ የሚያገኘው አገልግሎት እንዲቋረጥበት ይደረጋል።

## አንቀጽ አስራ አምስት
## መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ማሻሻል ወይም መለወጥ ይችላል።

## አንቀጽ አስራ ስድስት
## መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 29 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥቅምት 29 ቀን 1995 ዓ.ም**

**ካሡ ይላላ (ዶ/ር)**
**የመሠረተ ልማት ሚኒስትር**



www.chilot.me

# የቴሌኮሙኒኬሽን ሪሴል አገልግሎት ፍድ መጠየቂያ ቅፅ

1. የአመልካቹ ስም ____________________

2. ፍድ የተጠየቀበት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣

| የሪሴል አይነት | | አመልካቹ አገልግሎቱን ሊሰጥበት የፈለገው የስልክ መስመር ወይም የኢንተርኔት አካውንት ብዛት |
|---|---|---|
| • የስልክ ሪሴል አገልግሎት | ☐ | ____________ |
| • የፋክስ ሪሴል አገልግሎት | ☐ | ____________ |
| • የኢንተርኔት ሪሴል አገልግሎት | ☐ | ____________ |
| • የቴሌሴንተር አገልግሎት | ☐ | ስልክ____________<br>ፋክስ ____________<br>ኢንተርኔት____________ |

3. አገልግሎቱ የሚሰጥበት አድራሻ፣

ክልል____________________ ፖ.ሣ.ቁ____________________
ወረዳ____________________ ስልክ ቁጥር____________________
ከተማ____________________ ፋክስ____________________
ቀበሌ____________________ ኢ.ሜይል____________________
የቤት.ቁጥር____________________

4. ለሚጠየቀው የሪሴል አገልግሎት ወይም የቴሌሴንተር አገልግሎት የሪሴል ውል ከኮርፖሬሽኑ ጋር መኖር አለመኖሩ ይገለፅ፣

| | አለ | የለም | የሪሴል ውል ካለ ቁጥር/ሮቹ ወይም የዩዘር ስም/ሞች ይገለፁ |
|---|---|---|---|
| ለስልክ ሪሴል አገልግሎት | ☐ | ☐ | ____________<br>____________ |
| ለፋክስ ሪሴል አገልግሎት | ☐ | ☐ | ____________<br>____________ |
| የኢንተርኔት ሪሴል አገልግሎት | ☐ | ☐ | ____________<br>____________ |

አመልካች ከዚህ በላይ ያቀረብኩት መረጃ ትክክለኛና እውነተኛ መሆኑን እያረጋገጥኩ በዚሁ መሠረት ፍድ እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ::

የአመልካች ሥም____________________
ፊርማ____________________
ቀን ____________________

ማሳሰቢያ፣

- አመልካቹ ነጋዴ ከሆነ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ለንግድ ስራ የተመዘገበበትን ዋና የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማያያዝ አለበት::
- አመልካቹ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ከሆነ ደግሞ ሕጋዊ ሰውነት ያገኘበት ሰርተፊኬት ማያያዝ አለበት::
- ብዛታቸው 2 የሆኑ የአመልካቹ ወይም አመልካቹ የንግድ ማህበር ከሆነ የሥራ አስኪያጁ ፎቶግራፎች መያያዝ አለባቸው::
- አመልካቹ የሪሴል አገልግሎት ውል ከኮርፖሬሽኑ ጋር ከተዋዋለ ውሉን ማያያዝ አለበት::
- በአንድ ቅፅ ማመልከት የሚቻለው አንድ አድራሻ ውስጥ ለሚሰጥ የሪሴል ወይም የቴሌሴንተር አገልግሎት ብቻ ነው::
- አመልካቹ በየዓመቱ ከሐምሌ 30 በፊት ፍቃዱን ካላሳደሰ ፍቃዱ ይሰረዛል::



www.chilot.me

# የቴሌኮሙኒኬሽን ሪሴል

# አገልግሎት ውል

ይህ ውል በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን /ከዚህ በኋላ «ኮርፖሬሽን» ተብሎ በሚጠራው/ እና ____________ /ከዚህ በኋላ «ሪሴለር» ተብሎ በሚጠራው/ መካከል ዛሬ __________ /ቀን/ ዓ. ም. ተፈረመ።

## አንቀፅ አንድ

## የውሉ ዓላማ

የውሉ ዓላማ

ይህ ውል ሪሴለሩ

| የሪሴሉ ዓይነት | ብዛት | የስልክ ቁጥር /ሮች/ | የኢንተርኔት ተጠሚ መለያ ስም /ስሞች/ | አገልግሎቱ በኔትወርክ የተደገፈ ከሆነ የተገናኙ ኮምፒውተሮች ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| ☐ የስልክ | | | | |
| ☐ ኢንተርኔት | | | | |
| ☐ የፋክስ | | | | |

## አንቀፅ ሁለት

## የኮርፖሬሽኑ ግዴታ

### ኮርፖሬሽኑ:

ሀ. ለሪሴል የሸጠው አገልግሎት በብልሽት ሲቋረጥ ከ2 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይጠግናል።

ለ. ተጨማሪ የቴሌኮሙኒኬሽን ሪሴል አገልግሎት በሪሴለሩ ሲጠየቅ አገልግሎቱን ለመስጠት አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል።

ሐ. ሲስተሙን ለማሻሻል /upgrading/ ወይም የመከላከል ጥገና /preventive maintenance/ ለማድረግ አገልግሎቱን ማቋረጥ የግድ በሆነ ጊዜ ለሪሴለሩ ከ7 ቀናት በፊት ይህንኑ በጽሁፍ ያስታውቃል።



www.chilot.me

# አንቀፅ ሦስት

# የሪሴለሩ ግዴታ

**ሪሴለሩ:**

ሀ. ከኮርፖሬሽኑ በሚቀርብለት ኢንቮይስ ወይም ደረሰኝ መሰረት ኢንቮይሱ ወይም ደረሰኙ በደረሰው በ7 ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን የአገልግሎት ሂሳብ ይከፍላል::

ለ. ስለቴሌኮሙኒኬሽን በወጣው አዋጅ ቁጥር 49/1989 /እንደተሻሻለው/ የተከለከሉ አገልግሎቶችን መስጠት አይችልም::

ሐ. ሪሴል የሚያደርገው አገልግሎት ሲቋረጥበት ለኮርፖሬሽኑ በጽሁፍ ያስታውቃል::

መ. በዚህ ውል የገባውን ግዴታ ወይም ያገኘውን መብት ለሌላ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይችልም::

# አንቀፅ አራት

# ውል የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

1. ሪሴለሩ በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ የተሰጠው ፍቃድ በማናቸውም ምክንያት ከተሠረዘ ይህ ውል ፈራሽ ይሆናል::

2. ሪሴሌሩ በዚህ ውል አንቀፅ 3 /ሀ/ መሠረት የሚፈለግበትን አገልግሎት ሂሳብ ካልከፈለ ኮርፖሬሽኑ ውሉን ሊሠርዝ ይችላል::



www.chilot.me

## አንቀፅ አምስት

## ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች

1. ስለአቅም በላይ ሁኔታዎች በኢትዮጵያ በፍትሀብሄር ሕግ የተደነገገው በዚህ ውል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

2. ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አጋጥሞት ግዴታውን ያልተወጣ ወገን በሀላፊነት አይጠየቅም።

## አንቀፅ ስድስት

## ውሉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ውል ከዛሬ ________________ /ቀን/ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

________________________ ________________________

ስለኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ስለረሲለሩ

እማኞች፡

1. ስም________________ 2. ስም________________

ፊርማ____________ ፊርማ________________



www.chilot.me

## ለቋሚ የስልክ አገልግሎቶች የሚያገለግል
## የሪሴል ታሪፍ ሰንጠረዥ

| የመደበኛ ስልክ አገልግሎት | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን (ኢ.ቴ.ኮ) የመሸጫ ዋጋ /በብር/ | ሪሴለሩ የሚሸጥበት ጠቅላላ ዋጋ /በብር/ |
|---|---|---|
| በአንድ ከተማ ውስጥ ለሚደረግ ጥሪ (Local call) | ብር 0.20 በ3 ደቂ. | ብር 0.40 በ3 ደቂ. |
| ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ለሚደረግ ጥሪ (Long distance call) | የኢ.ቴ.ኮ ታሪፍ | የኢ.ቴ.ኮ ታሪፍ + ብር 0.30 በደቂ. |
| ለአለም አቀፍ ጥሪ (International call) | የኢ.ቴ.ኮ ታሪፍ | የኢ.ቴ.ኮ ታሪፍ + ብር 0.95 በደቂ. |
| ወደ ሞባይል ለሚደረግ ጥሪ | የኢ.ቴ.ኮ ታሪፍ | የኢ.ቴ.ኮ ታሪፍ + ብር 0.25 በደቂ. |

www.chilot.me